ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ     ረጀብ 17/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስቴር    ፌብሮዋሪ 18/2022 ግ.

# በኢስራእና ሚዕራጅ ያሉት ያአላህ ተላላቅ ታምራቶች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

{سُبْحَانَ الَّذِي أَسْرَى بِعَبْدِهِ لَيْلًا مِنَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ إِلَى الْمَسْجِدِ الْأَقْصَى الَّذِي بَارَكْنَا حَوْلَهُ لِنُرِيَهُ مِنْ آيَاتِنَا إِنَّهُ هُوَ السَّمِيعُ الْبَصِيرُ}

ለአለው ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጸዋ ትርጉም፡
( ያ ባሪያውን ከተከበረው መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደ ባረክነው ወደ ሩቁ መስጊድ በሌሊት ውስጥ ያስኼደው (ጌታ) ጥራት ይገባው፡፡ ከተዓምራቶቻችን ልናሳየው (አስኼድነው)፡፡ እነሆ እርሱ (አላህ) ሰሚው ተመልካቺው ነው፡፡)
አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል
የኢስራእና የሚዕራጅ ጉዞ ወሰን የለሹን የአላህ(ዐ.ወ.)ን ችሎታ የሚያሳይ ታላቅ ታአምር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ምክንያትንና በምክንያት የሚከሰቱ ነገሮችን የፈጠረ በመሆኑ በሰው ልጅ ዘንድ አስገራሚ የሆኑ ነገሮች ሁሉ ከሱ ዘንድ አስደናቂ እይደሉም፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{ِنَّمَا أَمْرُهُ إِذَاَ رَادَ شَيْئًاَ نْ قُيَ ولَ لَهُ كُنْ فَيَكُونُ}.**

(ነገሩም አንዳችን በሻ ጊዜ ኹን ማለት ነው፡፡ ወዲያው ይኾናልም፡፡)

አላህ (ዐ.ወ.) በዚህ ጉዞ ከምድር ዓለም ወደሰማያት ዓለም እንዲያርጉ ወደመጨረሻይቱ ቁርቁራም እንዲደርሱ በማድረግ፣ ተላላቅ ታምራትንና ወሰንየለሽ አስደናቂ ችሎታውን በማሳየት ወዳጁን ሙስጦፋን (ሶ.ዐ.ወ.) በእርግጥ አግዞዋል፡፡

ከአዚህ ተላላቅ ታምራት ከፊሎቹን እኛ የምናውቃቸው ሲሆን በአንድ ሌሊት ከመስጊደል ሐራም ወደመስጊደል አቅሷ እንዲጓዙ ማድረጉ፣ ከዚያም ወደላይኛዎቹ ሰማያት እንዲወጡ ማደረጉ ከዚያም እንደገና ወደመስጊደለ አቅሳና በመጨረሻም ወደመስጊደል ሐራም እንዲመለሱ ማድሩ የሚሉት ይካተቱባቸዋል፡፡ ይም የአላህን ወሰንየለሽ ችሎታ የሚያሳይ እንጂ ሌላ ነገር አይደልም፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሰማያት ዓለም ከአስደናቂ የአላህ ችሎታዎች ያዩትን አይተዋል፡፡ የተከበረው ቁርአን የአላህን ተላላቅ ታምራት እንድንመለከት እንድህ በማለት ይጠቁማል፡

**{ سَنُرِيهِمْ آيَاتِنَا فِي الآفَاقِ وفِيَ أَ فْ ُسِهِمْ حَتَّى يَتَبَيَّنَ لَهُمْ أَ نَّهُ الحَقُّ}.**

(እርሱም (ቁርአን) እውነት መኾኑ ለእነርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ተዓምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፡፡)

**አላህ (ዐ.ወ.) ቡራቅን ለንብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) መግራቱ ከነዚህ ተላላቅ ታምራት አንዱ ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (ቡራቅ ለኔ መጣልኝ፡፡ እሱም እግሩን ዓይኑ ከሚያርፍበት መጨረሻ የሚያስቀምጥ ረጂም ነጭ የጭነት ከብት ነው)፡፡**

**በዚህም ከታላቁ አላህ ታምራት ብዙ ነገር እንረዳለን፡፡ እንድሁም ለነገሮች ሰበብን ማድረስ እንደሚገባ ለነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ትምህርት**

**ሰጥቷል፡፡አላህ (ሱ.ወ.) ያለመንቀሳቀሻና ከነመሰሩት ያለሰበብ ይህን ጉዞ ማከናውን ይችል ነበርና፡፡**

**ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.)ከነብያትና ከአለህ መልእክተኞች ጋር መገናኘታቸው ሌላው እኛ ያወቅነው የዚህ ጉዞ ታምር ነው፡፡ በዚህም ነብያትን ሕያው በማድረግ የአለው የአላህ ችሎታ በግልጽ የታየበት ሲሆን በአቅሷ መስጊድ ከነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በኋላ እንድሰግዱ፣ ከከፊሎቹም ጋር በላይኛዎቹ ሰማያት እንዲገናኙና ሁላቸውም መልካም አቀባበል አድርገውላቸው መልካም ጸሎት እንዳደርጉላቸው አድርጓል፡፡ ይህም ከአላህ ጋር የገቡትን ቃል ያከበሩበት ተግባር ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡**

**{ وَإِذْ أَخَذَ اللَّهُ مِيثَاقَ النَّبِيِّينَ لَمَا آتَيْتُكُمْ مِنْ كِتَابٍ وَحِكْمَةٍ ثُمَّ جَاءَكُمْ رَسُولٌ مُصَدِّقٌ لِمَا مَعَكُمْ لَتُؤْمِنُنَّ بِهِ وَلَتَنْصُرُنَّهُ قَالَ أَأَقْرَرْتُمْ وَأَخَذْتُمْ عَلَى ذَلِكُمْ إِصْرِي قَالُوا أَقْرَرْنَا قَالَ فَاشْهَدُوا وَأَنَا مَعَكُمْ مِنَ الشَّاهِدِينَ}.**

(አላህ የነቢያትን ቃል ኪዳን ከመጽሐፍና ከጥበብ ሰጥቻችሁ ከዚያም «ከእናንተ ጋር ላለው (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ መልክተኛ ቢመጣላችሁ በርሱ በእርግጥ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል በያዘ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ አረጋገጣችሁን በዚህም ላይ ኪዳኔን ያዛችሁምን» አላቸው፡፡ «አረጋገጥን» አሉ፡፡ «እንግዲያስ መስከሩ፤ እኔም ከእናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ» አላቸው፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) በሰማይ ያለውን የደመቀውን ቤት ማየታቸው ደግሞ ሌላው እኛ ያወቅነው የኀዘው ታምር ነው፡፡ ነብያችን እንድህ ይላሉ፡ በዚያን ጊዜ ኢብራሂም በጀርባቸው የደመቀውን ቤት ተደግፈው አያሁ፡፡ በሱም በየቀኑ ሰባ ሺህ መላእኮች ወደሱ እንደገና የማይመለሱ ሲሆን የሚገቡበት መሆኑን አወቅሁኝ፡፡) ለዚህ ቤት ያለውን ክብርና ታላቅነቱን ለመግለጽ አላህ እንድህ በማለት ምሎበታል፡

**{وَالبَيْتِ المَعْمُورِ}.**

**(በደመቀው ቤትም)**

***ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ወደመጨረሻይቱ ቁርቁራ መድረሳቸው ሌላው እኛ ያወቅነው ታምር ነው፡፡ ይህም አላህ ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ከሰጣቸው ክብር አንዱ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡***

**{مَا كَذَبَ الْفُؤَادُ مَا رَأَى * أَفَتُمَارُونَهُ عَلَى مَا يَرَى * وَلَقَدْ رَآهُ نَزْلَةً أُخْرَى * عِنْدَ سِدْرَةِ الْمُنْتَهَى * عِنْدَهَا جَنَّةُ الْمَأْوَى * إِذْ يَغْشَى السِّدْرَةَ مَا يَغْشَى }.**

(ነቢዩም በዓይኑ) ያየውን ልቡ አልዋሸም፡፡ ታዲያ በሚያየው ላይ ትከራከሩታላችሁን? በሌላይቱም መውረድ ጊዜ በእርግጥ አይቶታል፡፡ በመጨረሻይቱ ቁርቁራ አጠገብ፤ እርሷ ዘንድ መኖሪያይቱ ገነት ያለች ስትኾን፡፡ ቁርቁራይቱን የሚሸፍን ነገር በሚሸፍናት ጊዜ (አየው)፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

የኢስራእና የሚዕራጅ ጉዞ ለበርካታ ፈተናዎችና ችግሮች ከተዳረጉ በኋላ ከፈጣሪ ለንብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የተቸረ ክብር ነው፡፡ እሱም ጭንቅን የሚያስወግድ፣ ልብን የሚያጠነክርና የመንፈስን ሚያረጋጊያ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{فَإِنَّ مَعَ الْعُسْرِ يُسْرًا * إِنَّ مَعَ الْعُسْرِ يُسْرًا}.**

(ከችግርም ጋር ምቾት አልለ፡፡ ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አልለ፡፡)

በዚህ ጉዞ እርሱ ከርሳቸው ጋር መሆኑን እንድሁም የእርሱ መመኪያነትና ጥበቃ ከርሳቸው ጋር መሆኑን ለማሳወቅ አላህ (ሱ.ወ.) ለሰው ልጅ የማይታወቁ እውነቶችንና መለኮታዊ ምስጥሮችን ለነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አሳውቆበታል፡፡

ቡሲሪ የተሠኙት የመንዙማ ገጣሚ የሚከተሉትን ግጥሞች በመድረሳቸው እጅጉን ይደነቃሉ፡

ጨረቃ በጨለማ ሌሊት እንደተጓዘ ሁሉ

በአንድ ሌሊት ከሐረም ወደሐረም ተጉዘሃል፡፡

ከደረጃ ወደረጃ ከተሸጋገርህ በኋላ ማንም ያላገኘውንና ያላሰበውን ከአንድ ደጋን  ጫፎች የቀረበን ደረጃ አግኝተሃል፡፡

በሱም ከነብያት ሁሉ ተቀዳሚ ሆነሃል፡፡

ከመልእክተኞችም ሁሉ ተገልጋይ ከአገልጋይ በመቀደም መልኩ ተቀዳሚ ሆነሃል፡፡

ጌታችን ሆይ በዚህች ዓለም በነብያችን በመልካም መከተልንና በመጭው ዓለም ደግሞ የሳቸውን ታዳጊነት ለግሰን፡፡ አሚን፡፡